**አዋጅ ቁጥር -----2017**

**የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ክፍያ አዋጅ**

ኢትዮጵያ ተለያይነት ባላቸው ሥርዓተ ምህዳሮች የበለፀገች እና እነዚህ ሥርዓተ ምህዳሮች በሀገራዊ የልማት ጥረቶች ላይ ያላቸውን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና አካባቢያዊ አስተዋፅኦ ማሳደግ በማስፈለጉ፤

እነዚህ ሥርዓተ-ምህዳሮች ዘላቂ ባልሆነ የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም ምክንያት በከፍተኛ ጫና ውስጥ በመሆናቸው ሥርዓተ ምህዳርን በዘላቂነት ለማስተዳደር የሚያስችል የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ክፍያ የህግ ማዕቀፍ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የፌደራል እና የክልል ተቋማት፣ የግሉ ዘርፍ እና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ልዩ ፍላጎት እና ሁኔታ ከግምት ውስጥ ያስገባ የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ክፍያ የአሰራር ሥርዓቶችን መዘርጋት በማስፈለጉ፤

በመሆኑም በኢትዮጲያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ-መንግስት አንቀፅ 55(1) እና አንቀፅ 51(5) ላይ የተቀመጠውን መሰረት አድርጎ ይህ አዋጅ ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ክፍያ አዋጅ ቁጥር ------2017" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጓሜ የሚሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

1/ "ሥርዓተ ምህዳር" ማለት ዕፅዋት ፣እንስሳትና በዓይን የማይታዩ ጥቃቅን ነብሳት በአካባቢያቸው ካለ ህይወት ከሌለው ነገር ጋር ያላቸው ተለዋዋጭ እና ውስብስብ መስተጋብር ነው፤

2/ "የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት" ማለት ሥርዓተ ምህዳር ለሰው ልጆች እና ለኢኮኖሚ የሚያበረክተው አስተዋፅኦ ነው፤

3/ "የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ክፍያ" ማለት አንድ የተወሰነ የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ወይም የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎቱን ለማግኘት የሚያስችለውን የመሬት አጠቃቀም አንድ ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ገዥዎች አንድ ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ሻጮች ሲገዛ እና ሻጭ አገልግሎቱን በዘላቂነት የሚያቀርብበት በተዋዋይ ወገኖች ፈቃድ የሚከናወን ግብይት ነው፤

4/ "ጥቅል የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት" ማለት ከአንድ በላይ የሆነ የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት አቅርቦት ላይ ትኩረት ያደረገ የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ክፍያ ስምምነት ነው፤

5/ "ገዥ" ማለት የሥርዓተ ምህዳር አግልጋሎቱ ተጠቃሚ የሆነ እና ለሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ወይም ለመሬት አጠቃቀም አሰራሩ እንዲጠበቅ፣ እንዲያድግ ወይም እንዲያገግም ላደረገው ሻጭ ለመክፈል ፈቃደኛ የሆነ ሰው ነው፤

6/ "ሻጭ" ማለት ከመሬት ወይም ከተፈጥሮ ሀብት ጋር በተያያዘ ባለመብት የሆነ እና ከገዥ ክፍያ የሚቀበል ነው፤

7/ “አደራዳሪ” ማለት በገዥና በሻጭ መካከል የሚደረጉ የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ክፍያ ስምምነት በማመቻቸት የተለያዩ ሚናዎችን እንዲጫወት በባለሥልጣኑ የተፈቀደለት ሰው ነው፤

8/ “የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት መነሻ ልኬት” ማለት የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ክፍያ ስምምነት በሌለበት ሁኔታ ከአንድ ሥርዓተ ምህዳር ሲገኝ የነበረ የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ደረጃ ነው፤

9/ “የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ተጨማሪነት” ማለት የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ክፍያ ስምምነት ከመፈፀሙ አስቀድሞ ከነበረ ሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት መነሻ ልኬት ላይ የጨመረ የሥርዓተ-ምህዳር አገልግሎት ማሻሻያ ነው፤

10/ “ቅድመ ሁኔታ” ማለት ከ አንድ ሥርዓተ ምህዳር ሊገኝ የታቀደው የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ውጤት ማስገኘቱ የሚረጋገጥበትና ክፍያ ለመክፈል የሚያስችል መስፈርት ነው፤

11/ “ያልታሰበ ተፅዕኖ” ማለት ከሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ክፍያ ስምምነት ከሚፈፀምበት ጂኦግራፊያዊ ክልል ውጭ በስምምነቱ አፈፃፀም ምክንያት የሚከሰት ተፅዕኖ ነው፤

12/ “ዘላቂነት” ማለት የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ስምምነት በሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት አቅርቦት ላይ የሚኖረው ማሻሻያ ሲሆን ከስምምነቱ ዘመን በላይ የሚኖር ማሻሻያን የሚጨምር ነው፤

13/ “ውጤት ተኮር ክፍያ” ማለት በተረጋገጠ የሥርዓተ ምህዳር አቅርቦት መሰረት የሚፈፀም ክፍያ ነው፤

14/ “ግብዓትን መሰረት ያደረገ ክፍያ” የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት አቅርቦት ለመጨመር የመሬት አጠቃቀም ሥርዓቶችን ትግበራ መነሻ በማድረግ የሚፈፀም ክፍያ ነው፤

15/ “የሥርዓተ ምህዳር ሁኔታ” በሥርዓተ ምህዳሩ ህይወት ባላቸው እና በሌላቸው ባህርይ ልኬት መሰረት የሥርዓተ ምህዳሩ ደረጃ ነው፤

16/ “ሚኒስቴር” ማለት የፕላንና ልማት ሚኒስቴር ነው፤

17/ “ባለሥልጣን” ማለት የፌደራል አካባቢ ጥበቃ ባስልጣን ነው፤

18/ “የክልል ባለስልጣን” ማለት ማንኛውም በክልል ደረጃ ያለ የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ክፍያ ለማስተዳደር ሀላፊነት የተሰጠው ተቋም ነው፤

19/ “ሰው” ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

20/ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው የሴትንም ፆታ ይገልፃል፡፡

3. **የተፈፃሚነት ወሰን**

ይህ አዋጅ በሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ሻጮች፣ ገዥዎች፣ አደራዳሪዎች እና በዚህ አዋጅ አባሪ 1 ስር በተዘረዘሩት የሥርዓተምህዳር አገልግሎት አይነቶች ላይ በሁሉም የኢትዮጵያ ግዛት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት
## የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ክፍያ መርሆዎች እና መልክዓ-ምድራዊ ሽፋን

4. **የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ክፍያ መርሆዎች**

ማንኛውም የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ክፍያ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መርሆዎች መከተል ይኖርበታል ፡-

1/ ገዥና ሻጭ የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ዋጋ ስምምነት በፍቃደኝነት የሚገቡ መሆኑ፤

2/ ገዥ ክፍያውን በቀጥታ ለሻጭ የሚከፍል መሆኑ፤

3/ ክፍያ የሚፈፀመው አንድ የተወሰነ ሥርዓተ-ምህዳር ሁኔታን የማሻሻል፣ የመጠበቅ አላማ ለሚያደርጉ የመሬት አያያዝ ሥርዓቶች መሆኑ እና

4/ በአንድ አካባቢ ከሥርዓተ-ምህዳር አገልግሎት ተጠቃሚ የመሆን ሂደት በሌላ አካባቢ ያልታሳበ ተፅዕኖ የማያስከትል መሆኑ፡፡

5. **የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ክፍያ መልክዓ- ምድራዊ ሽፋን**

ለሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ክፍያ ስምምነት ከዚህ በታች በተዘረዘሩት መልክዓ- ምድራዊ ሽፋን መሰረት ሊሆን ይችላል፡-

1/ ዓለም አቀፍ

2/ ሀገር አቀፍ

3/ ተፋሰስ ወይም

4/ ወረዳ

## ክፍል ሦስት

## ጥቅል የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት እና የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ክፍያ ስምምነት ይዘት

### 6. ጥቅል የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት

1/ የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ክፍያ ስምምነት ከአንድ ሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት በላይ አላማ ሊያደርግ ይችላል፡፡

2/ የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ክፍያ ስምምነት ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ጥቅል የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት አይነቶችን ታሳቢ ሊያደርግ ይችላል፡-

ሀ) አንድ ገዥ ከአንድ ሥርዓተ ምህዳር የሚገኙ ሙሉ አገልግሎቶችን ለማግኘት ክፍያ ሲፈፀም፤

ለ) ከአንድ በላይ ገዥዎች ከአንድ ሥርዓተምህዳር የሚገኙ አገልግሎቶችን ለማግኘት በተናጠል ለሻጮች ክፍያ ሲፈፅሙ፤

ሐ) ከአንድ ሥርዓተ ምህዳር የሚገኙ አንድ ወይም የተወሰኑ የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎቶች ለገዥዎች የሚሸጥ ሲሆን ሌሎች የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎቶች ያለክፍያ በነፃ ሲቀርቡ ነው፡፡

### 7. የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ክፍያ ስምምነት ይዘት

ማንኛውም የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ክፍያ ስምምነት ይዘት ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ጉዳዮች መያዝ ይኖርበታል፡-

1/ የገዥ እና ሻጭ አድራሻና ሙሉ መረጃ፤

2/ የገዥ እና ሻጭ መብትና ግዴታዎች፡- የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎቶች የተሸጡበት የቦታው ባለቤትነት ሲለወጥ እና በመጀመሪያ ዋና ገዥ እና በማንኛውም ቀጣይ ገዥዎች የስርዓተ ምህዳር አገልግሎቱ እንደገና ሲሸጥ ያሉ ድንገተኛ ሁኔታዎች መካተት አለበት፤

3/ ስምምነቱ የሚፈፀምበት ቦታ ዝርዝር ሁኔታ፤

4/ የክፍያ አይነት፣ የአከፋፈል ሁኔታ እና ክፍያ ጊዜ፤

5/ የክትትል፣ የማረጋገጫ እና የሪፖርት መስፈርቶች ፤

6/ በስምምነቱ የተጠቀሱ ግዴታዎችን ያለማክበር ውጤቶች፤

7/ ስምምነት ስለሚሻሻልበት ሁኔታ፤

8/ ስምምነቱ ስለሚሰረዝባቸው ሁኔታዎች፤

9/ የስምምነቱ ዘመን፤

10/ ከአቅም በላይ በሆኑ ምክንያቶች በሚደርሱ ጉዳቶች ምክንያት የሚደርስ ኪሳራን ገዥ እና ሻጭ የሚጋሩበት ሁኔታ፤

11/ የግጭት አፈታት ዘዴ እና

12/ የተዋዋይ ወገኖች ፊርማ፡፡

## ክፍል አራት

## የአከፋፈል ሁኔታ፣ የፋይናንስ ምንጭ እና የጥቅም መጋራት

### 8. የአከፋፈል ሁኔታ

1/ ለሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት የሚከፈል ክፍያ በገዥና ሻጭ ስምምነት የሚወሰን ሲሆን አደራዳሪ የአከፋፈል ሁኔታዎችን ሊያመቻች ይችላል፡፡

2/ በሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ክፍያ ስምምነት መሰረት ክፍያ ተፈፃሚ የሚሆነው ለተረጋገጡ ውጤቶች ብቻ ነው፡፡

3/ ውጤት ተኮር ወይም ግብዓትን መሰረት ያደረገ ክፍያ ለሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ክፍያ ሊውል ይችላል፡፡

### 9. የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት የፋይናንስ ምንጭ

የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ክፍያ የገንዘብ ምንጮች ከዚህ በታች በተዘረዘረው መንገድ ሊሆን ይችላል፡-

1/ መንግስት ህዝብን በመወከል የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎትን ለማሳደግ መንግስት ለሻጭ የሚከፍልባቸው የመንግሰት ክፍያ መርሃ ግብሮች፤

2/ ግለሰቦች የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ለማግኘት በቀጥታ ለሻጭ ክፍያ የሚፈፅሙበት እና

3/ በመንግስትና በግለሰብ ጥምረት የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ለማግኘት ለሻጭ ክፍያ የሚፈፀምበት ነው፡፡

## 10. የጥቅም መጋራት

1/ ማንኛውም የጥቅም መጋራት ስምምነቶች የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ክፍያ ስምምነት በሻጭ እና በገዥ መካከል ከመፈረሙ አስቀድሞ መከናወን አለበት፡፡

2/ በሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ክፍያ ስምምነት በሻጮች መካከል የሚደረግ የጥቅም መጋራት ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ጉዳዮች ከግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርበታል፡-

ሀ) የጥቅም መጋራት ሂደቱ ውጤት ያስገኙ አካላትን የሚያበረታታ እና ዝቅተኛ አስተዋፅኦ ላላቸው በተመሳሳይ ዝቅተኛ ጥቅም የሚያስገኝ መሆን አለበት፤

ለ) ግልፅና ከአድሎ የፀዳ መሆኑ በባለድርሻ አካላት መወሰን አለበት፤

ሐ) የጥቅም መጋራት ሥርዓቱ በተቻለ መጠን የህብረተሰብ መሰረት ባላቸው ተቋማት ወይም ከሁሉም የህብረተሰብ ሰፊ ውክልና ያለው እና ህብረተሰቡን በውሳኔ ሰጪነት የሚያሳትፍ ተቋም መቋቋም አለበት፡፡

## ክፍል አምስት

## ክትትል፣ ሪፖርት እና ማረጋገጥ

## 11. ክትትል፣ ሪፖርት እና ማረጋገጥ

1/ የሥርዓተ-ምህዳር አገልግሎት ክፍያ ስምምነት አተገባበር በሻጭ ክትትል እየተደረገበት ለገዥው እና ለባለሥልጣኑ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ጉዳዮች ለማረጋገጥ ሪፖርት ይላካል፡-

ሀ) ከሥርዓተምህዳር አገልግሎት ክፍያ ስምምነት የሚጠበቁ ውጤቶች እየተገኙ መሆኑን፤

ለ) ክፍያ ግብዓትን መሰረት ያደረገ ከሆነ ግብዓቱ የሥርዓተ ምህዳሩን ሁኔታ በእርግጥ እያሻሻለ መሆኑን፤

ሐ) በስምምነቱ ከተሸፈነው አካባቢ ውጭ የሥነ-ምህዳሩን ሁኔታ ወይም የሥርዓተ-ምህዳር አገልግሎት አቅርቦት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የማያሳድር መሆኑን፤

መ) አግባብነት ያላቸው የቁጥጥር መስፈርቶች የተከበሩ መሆኑን፤

2/ በሥርዓተ-ምህዳር አገልግሎት ክፍያ ስምምነት መሰረት ተጨማሪ አገልግሎት እየተገኘ መሆኑን ክትትል ለማድረግ የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎቱ መነሻ መወሰን አለበት፡፡

3/ የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ክፍያ ስምምነት መሰረት በስምምነቱ ምክንያት አሉታዊ ተፅዕኖ ሊያደርስ የሚችልባቸውን አካባቢ መለየት አለበት፡፡

4/ የሻጭ የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ክፍያ ስምምነት አተገባበርን የመከታተልና ሪፖርት የማቅረብ ሀላፊነት በባለስልጣኑ ሲፈቀድ ለህዝባዊ ተቋም ወይም ለአደራዳሪ ሊተላለፍ ይችላል፡፡

5/ የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ክፍያ ስምምነት አተገባበር በየጊዜው በባለሥልጣኑ ፍቃድ በተሰጠው አረጋጋጭ መረጋገጥ አለበት፡፡

## <u>ክፍል ስድስት</u>
## <u>የባለስልጣኑ ኃላፊነት እና የአደራዳሪ ሚና</u>

### 12. <u>የባለስልጣኑ ኃላፊነት</u>

ባለሥልጣኑ ይህ አዋጅ በስራ ላይ እንዲውል ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ሀላፊነቶች ይኖሩታል፡-

1/ ለተለያዩ የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ክፍያ ስምምነት የሚውሉ የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት መነሻ ልኬት መወሰኛ እና የክትትል፣ የሪፖርት እና የማረጋገጫ የቴክኒክ መመሪያዎች ያዘጋጃል፤

2/ የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ክፍያ ስምምነት እና ተያያዥ የክትትል ሪፖርቶች የሚቀመጡበት መዝገብ ያደራጃል፤

3/ የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ክፍያ ስምምነት የክትትል ሪፖርቶችን በመገምገም የጥራት ማረጋገጫ ያከናውናል፤

4/ ለአደራዳሪዎች ፍቃድ ይሰጣል፣ ፍቃድ የተሰጣቸው የአደራዳሪዎች ዝርዝር የያዘ መዝገብ ያደራጃል፡፡

### 13. <u>የአደራዳሪ ሚና</u>

1/ አደራዳሪ በሥርዓት ምህዳር አገልግሎት ክፍያ ስምምነት ላይ የሚከተሉትን ሚናዎች ሊኖሩት ይችላል፡-

ሀ) ሻጭ የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ዋጋ ትመና ላይ እና ለገዢዎች እንዲቀርብ መርዳት፤

ለ) ገዥና እና ሻጭን ማስተዋወቅና እና በመካከላቸው መልካም ግንኙነት መፍጠር፤

ሐ) የሥርዓተ-ምህዳር አገልግሎት መነሻ ልኬት እና የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ተጨማሪነት ወሰን ማቋቋም፤

መ) ዋጋዎችን ለመወሰን ፣ የገንዘብ ድጎማዎችን ለማግኘት፣ ስምምነቶችን በማዘጋጀት እና በጋራ ተቀባይነት ባለው የክፍያ ሥርዓት ላይ ማስማማት፤

ሠ) በክትትል ፣ በሪፖርት እና በማረጋገጥ ላይ መርዳት።

2/ አደራዳሪ በባለሥልጣኑ ፍቃድ የተሰጠው እና የተመዘገበ መሆን አለበት።

## ክፍል ሰባት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 14. ግዴታን አለማክበር

1/ በዚህ አዋጅ የተቀመጡ ግዴታዎች ያልተከበሩ እንደሆነ ባለስልጣኑ የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ክፍያ ስምምነትን የመሰረዝ ወይም የመቅጣት ወይም ሁለቱንም ማድረግ ይችላል።

2/ ገዥና ሻጭ ከአቅም በላይ የሆኑና ሊወገዱ የማይችሉ ችግሮች እንደ በተባይ መወረር ፤ የዝናብ ሁኔታ መለዋወጥና የተፈጥሮ የእሳት አደጋ ያሉ ክስተቶች ምክንያት ጉዳት ሲከሰት ችግሮችን የሚጋሩበት ሁኔታዎች ላይ መስማማት ይኖርባቸዋል።

### 15. በስራ ላይ የሚገኙ የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ክፍያ ስምምነቶች

1/ ይህ አዋጅ በስራ ላይ ከመዋሉ በፊት ከሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ክፍያ ስምምነት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ፕሮጀክቶች ላይ ተፈፃሚ አይሆንም።

2/ በዚህ አዋጅ ንዑስ አንቀፅ (1) የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ክፍያ ስምምነት ላይ እድሳት ወይም ማሻሻል የሚፈፀመው በዚህ አዋጅ መሰረት መሆን አለበት።

## 16. ደንብና መመሪያ የማውጣት ስልጣን

1/ የሚንስትሮች ምክር ቤት ለአዋጁ አፈጻጸም የሚረዱ ደንቦች ሊያውጣ ይችላል፡፡

2/ ባለሥልጣኑ ለአዋጁ አፈፃፀም የሚያግዙ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

አዲስ አበባ ------- ቀን ------/2017 ዓ/ም

ታዬ አፅቀስላሴ

የኢትዮጲያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዝዳንት

**አባሪ 1**

# የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት አይነቶች

| የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት<br>የሚሰጠው አገልግሎት | | መግለጫ |
|---|---|---|
| ባዮማስ የሚሰጣቸው አገልግሎቶች | ሰብል | -የሰብል ሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት፡-<br>- ሥርዓተ ምህዳሩ ሩ ሰብሉ እንዲያድግ አስተዋፅዎ ያደርጋል፡፡ ሰብሉ የሚሰጣቸው ጥቅሞች እንደ ምግብ ቃጫ ምርት ግጦሽ እና ሀይል ሰጪ የመጨረሻው የሥርዓተ ምህዳሩ አገልግሎቶች ናቸው፡፡ |
| | የግጦሽ ባዮማስ | -የግጦሽ ባዮማስ ሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ፡-<br>- ሥርዓተ ምህዳሩ ለከብቶች ግጦሽ የሚውል ግብዓት የግጦሽ ባዮማስ አስዋፅዎ ያደርጋል |
| | የከብት እርባታ | -የከብት እርባታ ሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት፡-<br>- ሥርዓተ ምህዳሩ የከብት እርባታና ከከብት እርባታ የሚገኙ ምርቶች እንዲያድግ ያደርጋል ይሄውም ኢኮነሚያዊ ጥቅም ያላቸው በዋነኛነት የምግብ ምርት ለምሳሌ፡- ወተት፣ ስጋ፣ እንቁላል ፣ ሱፍክር እና ቆዳ |
| | አኳካልቸር | -አኳካልቸር ሥርዓተ ምህዳር አገልግሎቶች፡-<br>- ሥርዓተ ምህዳሩ በውስጡ ላሉ እንስሳትና እፅዋት አስተዋፅዎ ያደርግላቸዋል፡፡ ለምሳሌ ፡- ዓሳ፣ ሼልፊሽ እና ሲዉድ |
| | እንጨት | -እንጨት ሥርዓተ ምህዳር አገልግሎቶች፡-<br>- ሥርዓተ ምህዳሩ ዛፎችና ሌላ እንጨትነክ ባዮማስ ፣ የተተከሉና በተፈጥሮ የበቀሉ ጥቅምላይ የዋሉ ምሳሌ፡- የጣውላ ምርት ስነ-ምህዳር አስተዋፅዎ ያደርግላቸዋል |
| | በተፈጥሮ ውሀ ውስጥ የሚኖሩ ዓሳና ሌሎች ባዮማስ | -በተፈጥሮ ውሀ ውስጥ የሚኖሩ ዓሳና ሌሎች ባዮማስ ሥርዓተ ምህዳር አገልግሎቶች ፡-<br>- ሥርዓተ ምህዳሩ በተፈጥሮ ውሀ ውስጥ የሚኖሩ ዓሳና ሌሎች ባዮማስ እንዲያድጉ አስተዋፅዎ ያደርግላቸዋል፡፡ እነኚሁ ተይዘው ለምግብነት ሲውሉ የመጨረሻ የስነ-ምህዳር አግልግሎት ይሆናሉ፡፡ |
| | የዱር እንስሳት እፅዋት እና ሌሎች ባዮማስ | -የዱር እንስሳት እፅዋት እና ሌሎች ባዮማስ ሥርዓተ ምህዳር አገልግሎቶች፡-<br>- ሥርዓተ ምህዳሩ የዱር እንስሳት እፅዋት እና ሌሎች ባዮማስ አንዲያድጉ አስተዋፅዎ ያደርግላቸዋል፡፡ |
| የዘረመልቁስ አገልግሎት | | የዘረመልቁስ አገልግሎት |
| የውሀ አቅርቦት፡- | | -የውሀ አቅርቦት ሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት፡-<br>- የውሀ ፍሰት ስርዓት፤ የውሀው ንፅህና |

| | | |
|---|---|---|
| | | እና ሌሎች የሥርዓተ ምህዳሩ አግልግሎቶች ለተጠቃሚ በትክክል ንፁህ ውሀ ለማቅረብ አስተዋፅዎ አላቸው፡፡<br>- የቤት ውስጥ ፍጆታ የመጨረሻ የስነ-ምህዳሩ አግልግሎት ነው፡፡ |
| የማስተካከልና የመጠገን አገልግሎት | | |
| የአፈር ጥራት የማስተካከል አገልግሎት | | -የአፈር ጥራት የማስተካከል ሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት፡-<br>- ሥርዓተ ምህዳሩ የአፈር ጥራት የማስተካከል አገልግሎት ማለትም ህይወት ያላቸውና ህይወት የሌላቸውን ቁሶች እንዲበሰብሱና የአፈሩ ለምነትና ፀባይ ላይ አስተዋፆ አለው፡፡ ምስሌ፡- የባዮማስ ግብዓት<br>- ይህ አብዛኛው ግዜ የሚመዘነው እንደ ኢንተርሚዴት አገልግሎት ነው፡፡ |
| አፈርና ደለልን የማቆየት አገልግሎት | የአፈር መሸርሸርን መቆጣጠር አገልግሎት | -የአፈር መሸርሸርን መቆጣጠር ሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት<br>- ይህ ሥርዓተ ምህዳር በተለይ ደን አፈር ተረጋግቶ እንዲቆይና የአፈር ብክለትን የሚቀንስ እና አካባቢን የሚደግፍ ነው ለምሳሌ፡- ለግብርና እና ለውሀ አቅርቦት የስነ-ምህዳሩ አስተዋፅዎ ወሳኝና የመጨረሻ ነው፡፡ |
| | የመሬት ናዳ የመቀነስ አገልግሎት | -የመሬት ናዳ የመቀነስ ሥርዓተ ምህዳር ፡-<br>- በሥርዓተ ምህዳሩ በተለይም የደን ውድመትን በመከላከል በአፈር ፣ በድንጋይና በበረዶ ናዳ በሰው ልጅ ጤናና ደህንነት እና በመሰረተ ልማት ውድመት ላይ የሚደርሰውን ጉዳት በመቀነስና በማስቀረት የሚያደርገው አስተዋፅዎ የመጨረሻ የስነ-ምህዳር አገልግሎት ነው፡፡ |
| የደረቅ ቆሻሻ ማከም አገልግሎት | | -የደረቅ ቆሻሻ ማከም ሥርዓተ ምህዳር ፡-<br>- በሥርዓተ ምህዳሩ ጥቃቅን በዓይን የማይታዩ ነብሳት ፣ አልጌ፣ እፅዋትና እንስሳት ያላቸውን ጉዳት ለመቀነስ በሚወሰደው እርምጃ ህይወት ያለውና ህይወት የሌለው ነገር መለወጥ የስነ-ምህዳሩ የመጨረሻ የማስማሚያ አገልግሎት ነው፡፡ |

| | | |
|---|---|---|
| ውሀን የማጥራት አገልግሎት (የውሀን ጥራት መቆጣጠር) | ማቆየትና የንጥረ-ነገሮች መሰባበር<br><br>ማቆየትና የበካይ-ነገሮች መሰባበር | -ውሀን የማጥራት ሥርዓተ ምህዳር ፦<br>- ሥርዓተ ምህዳሩ ንጥረ-ነገሮችና ሌሎች በካይ ነገሮች በማስወገድ በመሬት ላይ እና ከመሬት በታች የሚገኝ ውሀን ኬሚካላዊ ሁኔታን በመመለስ ያስተካክላል፡፡<br><br>-ውሀን የማጥራት ሥርዓተ ምህዳር ፦<br>- በሥርዓተ ምህዳሩ በሰው ልጅ ላይ ጉዳት የሚያደርሱ የተበከሉ ነገሮች ጉዳት መቀነስ የመጨረሻ የሥርዓተ ምህዳሩ አገልግሎት ነው፡፡ |
| የውሃ ፍሰትን የማሰተካከል አገልግሎት | ከመነሻ መስመር ፍሰትን የማስተካከል/የመጠገን አገልግሎት | -የውሃ ፍሰትን የማሰተካከል ሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ፧-<br>- የወንዝ ፍሰት፣ ከመሬ በታች ያለ ውሀና የሐይቆችን የውሀ ወለል ማስተካከል የሥርዓተ ምህዳሩ አስተዋፅዎ ነው፡፡<br>- የሥርዓተ ምህዳሩ ውሀን መጦ ማስቀረት፧ ማከማቸትና በድርቅ ወቅት በትነት መልክ እየለቀቀ የውሀ መጠንን የማሰተካከል ችሎታ አለው፡፡ ይህም የመጨረሻ የሥርዓተ ምህዳርአገልግሎት ተብሎ ሊመዘገብ ይችላል፡፡ |
| | በከፍታ መፍሰስን የመቀነስ አገልግሎት | -የውሃ ፍሰትን የማሰተካከል ሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ፧-<br>- ስነ-ምህዳሩ ውሀን መጦ ማስቀረት፧ ማከማቸትና የጎርፍና ሌላ ውሀ ከመጠን በላይ ሲሆን የሚደርስ አደጋን በመቀነስ ባለው ችሎታ የወንዝ ፍሰት፣ ከመሬ በታች ያለ ውሀና የሐይቆችን የውሀ ወለል ማስተካከል የስነ-ምህዳሩ አስተዋፅዎ አለው፡፡<br>- ውሀን በከፍታ መፍሰስንና ጎርፍን የመቀነስ አገልግሎት የመጨረሻ የስነ-ምህዳሩ አገልግሎት ነው፡፡ |
| ጎርፍ የመቆጣጠር አገልግሎት | ጎርፍየመከላከል አገልግሎት፦ | -ጎርፍየመከላከል ሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት፦<br>- በስነ-ምህዳሩ የባሕር ዳረቻ አካላት ለምሳሌ፦ ኮራልሪፍ፣ሳንድ ባንክስ፣ ዱኒ ወይም ማንግሩቭ ሲስተም በባሕር ዳረቻ አካባቢ ያለውን ህ/ሰብ ከሀይለኛ አውሎ-ንፋስ መከላከል የመጨረሻ የስነ-ምህዳሩ አገልግሎት ነው፡፡ |

| | | |
|---|---|---|
| | የወንዝ ሙላት የመቀነስ አገልግሎት፡- | -የወንዝ ሙላት የመቀነስ ሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት፡-<br>- በሥርዓተ ምህዳሩ የወንዝ ዳረቻ ደኖች በአቀማመጣቸው ሀይለኛ የውሀ ሙላትን በመቀነስ የአካባቢውን ነዋሪ ከጎርፍ አደጋ ለመከላከል ይረዳሉ፡፡<br>- ሥርዓተ ምህዳሩ ውሀን በከፍታ መፍሰስንና ጎርፍን የመቀነስ አገልግሎት በጋራ ሆነው ጎርፍ የመከላከል አገልግሎት ይሰጣሉ፡፡ ይህ የመጨረሻ የስነ-ምህዳሮቹ አገልግሎቶች ናቸው፡፡ |
| -ሀይለኛ አውሎነፋስ የመቀነስ አገልግሎት | | -ሀይለኛ አውሎነፋስ የመቀነስ ሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት፡-<br>- ደኖች ከባሕር ዳረቻ አካላት ጋር በመሆን ንፋስ፣ አሻዋና ሌላ አውሎነፋስ በአካባቢ ያለውን ህ/ሰብ መከላከል የመጨረሻ የስነ-ምህዳሩ አገልግሎት ነው፡፡ |
| የድምፅ ብክለት መቀነስ አገልግሎት | | -የድምፅ ብክለት የመቀነስ ሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ፡-<br>- ህብረተሰብ ላይ ሚደርሰውን የድምፅ ተፅዕኖ ማለትም ጎጂነቱንና አስጨናቂነቱን መቀነስ የተለመደና የመጨረሻ የስነ-ምህዳሩ አገልግሎት ነው፡፡ |
| የአበባ ዘር ስርጭት አገልግሎት፡- | | -የአበባ ዘር ስርጭት ሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት፡-<br>- በዱር ብናኞች አማካኝነት ሰብሎችን በማሻሻል ወይም በመጨመር በሰፊው እንዲገኙ ወይም የተለያየ ሌላ ዝርያ እንዲኖራቸው ማድረግ የመጨረሻ የስነ-ምህዳሩ አገልግሎት ነው፡፡ |
| ሥነ-ሕይወታዊ ነገሮችን የመቆጣጠር አገልግሎት | ተባዮችን የመቆጣጠር አገልግሎት | -ሥነ-ሕይወታዊ ነገሮችን የመቆጣጠር ሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት፡-<br>- የዝርያዎች መከሰትን በመቀነስ ተባዮች በባዮማስ ምርት ሂደት ወይም ሌላ ኢኮኖሚያዊና የሰው ልጅ የሚያከናውናቸው ተግባራት ላይ የሚያመጡትን ተፅዕኖ ይቀንሳል ወይም ያስቀራል፡፡ |
| | በሽታን የመቆጣጠር አገልግሎት፡- | -በሽታን የመቆጣጠር ሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት፡-<br>- የዝርያዎች መከሰትን በመቀነስ ዝርያዎች በሰው ልጅ ጤንነት ላይ |

| | | |
|---|---|---|
| | | የሚያመጡትን ተፅዕኖ ይቀንሳል ወይም ያስቀራል፡፡ |
| የጨቅላዎች ቁጥር ብዛት እና የመኖሪያ ቦታ ጥገና አገልግሎት | | -የጨቅላዎች ቁጥር ብዛት እና የመኖሪያ ቦታ ጥገና ሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት፡-፡-<br>- ይሄውም ኢኮኖሚ ጥቅማችውን ያስገደብ ለመጠቀም ወይም የመኖሪያ ቦታቸውን በመጠገን (ምሳሌ፡- ለጨቅላዎች) ወይም የተፈጥሮ የጂን ፖሎችን በመከላከል ለዝርያዎች መብዛትና ዘላቂነት የሥርዓተ ምህዳር አስተዋፅዎ ወሳኝ ነው፡፡<br>- ይህ የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት አስታራቂና ምናልባትም ለተለያዩ የመጨረሻ የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎቶች እንደ ባዮማሳ አቅርቦትና ከመዝናኛ ጋር የተያያዘ አገልግሎት ግብአት ይሆናል፡፡ |
| ሌላ የመቆጣጠርና የመጠገን አገልግሎት | | |
| ባህላዊ አገልግሎት | | |
| ከመዝናኛ ጋር የተያያዘ አገልግሎት | | -ከመዝናኛ ጋር የተያያዘ ሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት፡-<br>- በተለይም ሥርዓተ ምህዳሩ ባዮፊዚካል ባህሪ እና ጥራት ላይ ተመርኩዞ ህ/ሰብ አካባቢያቸውን በቀጥታ፣ በመስክ/በዋናው ቦታ፣ በአካልና አካባቢን የመለማመድ ግንኙነታ በማድረግ መጠቀምና መዝናናት ያስችላል፡፡<br>- ይህ አገልግሎት በአቅራቢያ ያለ አካባቢና ከአካባቢ ውጪ(ጎብኖች፣ ቱሪስቶች) ያካትታል፡፡<br>- ከመዝናኛ ጋር የተያያዘ አገልግሎት አዝናኝ የሆነ ዓሳ ማጥመድና አደን ማደን በማቅረብ ማካሄድ ይቻላል፡፡ |
| የእይታ ምቹነት አገልግሎት | | -የእይታ ምቹነት ሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት፡-<br>- የአካባቢ አኗኗር ሁኔታ በተለይም ስነ-ምህዳር ባዮፊዚካል በሀሪ እና ጥራት ላይ ተመርኩዞ ስሜታዊ ጠቀሜታዎችን በተለይም ለእይታ ማዘጋጀት ይቻላል፡፡<br>- ይህ አገልግሎት መዝናኛን ጨምሮ ከሌላ ሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ጋር ይጣመራል፡፡ ፡፡ |

| | | |
|---|---|---|
| ትምህርት ሳይንሳዊና ጥናት አገልግሎት | | -ትምህርት ሳይንሳዊና ጥናት ሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት፡-<br>- ሥርዓተ ምህዳሩ በተለይም ባዮፊዚካል በሀሪ እና ጥራት ላይ ተመርኩዞ በአካባቢና ምሁራዊ መስተጋብር ህብረተሰቡ አካባቢውን እንዲጠቀም ያስችላል፡፡ |
| መንፈሳዊ ጥበባዊና ተምሳሌታዊ አገልግሎት | | -መንፈሳዊ ጥበባዊና ተምሳሌታዊ ሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት፡-<br>- ስነ-ምህዳሩ በተለይም ባዮፊዚካል በሀሪ እና ጥራት ላይ ተመርኩዞ ህብረተሰቡ ባህላዊ ታሪካዊ ውበትን የተቀደሰ ወይም የሀይማኖት አስፈላጊነትን እንዲገነዘብ ያደርጋል፡፡<br>- ይህ አገልግሎት ከስር ያለ ህ/ሰብ ባህላዊ ማንነትና ህብረተሰቡ እራሱን በተለያየ ጥበባዊ ሚድያ እንዲገልጥ ያነቃቃል፡፡ |